# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

ትንሣኤ በዋለ በስድስተኛው ሳምንት ሰንበት የሚከናወን ሥርዓተ አምልኮ

ዘመነ ትንሣኤ ወይም ፋሲካ የሚባለው ከጌታችን ትንሣኤ ጀምሮ እስከ ዕርገት ያሉት ቀኖች ናቸው። በእነዚህ ዕለታትና ሳምንታት የሚዘመሩት መዝሙራት ሞትን ትንሣኤን ስቅለትን የመሳሰሉትን የሚያነሱ ናቸው።

## የዕለቱ ምስባክ

እስመ ሰበረ ኆኃተ ብርት
ወቀጥቀጠ መናስግተ ዘኃፂን
ወተወክፎሙ እም ፍኖተ ጌጋዮሙ

የነሐሱን ደጆች ሰብሮአልና
የብረቱንም መወርወሪያ ቆርጧልና
ከበደል ጐዳና ተቀበላቸው

መዝ ፩፻፮፥፲፮

ትርጉም፥ ከአመጻቸው ተቀበላቸው መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን ሰራዊተ አጋንንትን አጥፍቶአልና መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን ሊቃነ አጋንንትን አጥፍቶአልና፤ ኃጢአት ሰርተው ከሄዱበት አገር ከሲኦል በልጅነት ከመከራ በንስሃ ተቀበላቸው።

ወንጌል፥ ዮሐ ፳፩፥፲፭-ፍጻሜ
ቅዳሴ፥ የዲዮስቆሮስ ቅዳሴ (እምቅድመ ዓለም)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

አርአየ ስልጣኑ ለእለ ሞት
«ስልጣኑን በሞት ላይ አሳየ»

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| ፩ | ሮሜ ፮፥፩-፩፭ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| ፪ | ፩ኛ ጴጥ ፬፥፬-፲፪ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| ፫ | የሐዋ ሥራ ፳፫፥፲፭-፳፪ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

### «ትወደኛለህን?»

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ ከተነሳ በኋላ በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ እንደገና ተገለጠላቸው። ተማሪዎቹ አሣ ለማጥመድ ወደ ወንዝ ሄደው ሌሊቱን ሁሉ ደክመው ምንም ባለማግኘታቸው ተስፋ ቆርጠው ሳሉ ክርስቶስ መጥቶ ባመለከታቸው ቦታ መረባቸውን በመጣላቸው እንደ ቃሉ ብዙ አሣዎችን እንዳገኙ፤ ጌታንም እንዳወቁት ከእርሱም ጋር እንደበሉ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሃያ አንድ ከቁጥር አንድ እስከ አሥራ አራት ላይ እናነባለን።

በዚሁ ምዕራፍ ከቁጥር አሥራ አምስት ጀምሮ ደግሞ ከማእዱ በኋላ መድኃኒታችን ለቅዱስ ጴጥሮስ «የዮና ልጅ ጴጥሮስ ስምዖን ሆይ! እነዚህ ከሚወዱኝ ይበልጥ ትወደኛለህን? አለው» ከዚህ በፊት ጴጥሮስ «ሌሎቹ ሁሉ እንኳ ቢክዱህ እኔ ከቶ አልክድህም» ሲል ተናግሮ ነበር (ማቴ ፳፮፥፴፫)። አሁን ግን እራሱን በሐሙስ ማታው ፈተና ስላወቀው፤ ከጓደኞቹ ይልቅ እወድሃለሁ ብሎ ጓደኞቹ ያላደረጉትን በደል (ክህደት) በጌታ ላይ ስለፈጸመ በፊሊጶስ ቂሳሪያ አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ባለበት አንደበቱ «ሰውየውን አላውቀውም» «የምትይውን አላውቀውም» ብሎ ስለካደ፤ በመከራው ጊዜ አብሮት ሊሆን ቀርቶ «የሕይወት ቃል ያለህ አንተን ትተን የት እንሄዳለን» ይል የነበረው ከእርሱ ጋር የነበረበትን የቀድሞውን ጊዜም ስለካደ በአጠቃላይ ራሱን በትክክል ስላወቀ አሁን «አዎ ጌታዬ ሆይ እኔ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ» ሲል መለሰ። የልቡን ሃሳብ የሚያውቀው ጌታ የእርሱን እውነተኛነት እንዲረዳለት ተማጸነ «አንተ ታውቃለህ» አለ። ጌታም «ግልገሎቼን ጠብቅ» አለው። እንደገናም ጥያቄውን በመድገም « … ትወደኛለህን?» ብሎ ደግሞ ጠየቀው። በዚህ ጊዜ ከሌሎቹ ደቀ መዛሙርት አብልጦ ይወደው እንደሆነ አልጠየቀም። ጴጥሮስም «አዎን ጌታዬ ሆይ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ» ብሎ መለሰ። ጌታም «ጠቦቶቼን ጠብቅ» አለው። ጌታም ለሦስተኛ ጊዜም መልሶ ጠየቀው «የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ትወደኛለህን?» አለው። እርሱም እንደ ልማዱ «እንድወድህ አንተ ታውቃለህ» አለው። መድኃኒታችንም «በጎቼን ጠብቅ» አለው።

ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን ሦስት ጊዜ ክዶት ስለነበር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የጴጥሮስን ፍቅርና ታማኝነት ለማረጋገጥ ሲል ልብን እንደ ቀስት የሚወጋ ሦስት ቀጥተኛ የሆኑ ጥያቄዎችን ጠየቀው። ቅዱስ ጴጥሮስ ከጓደኞቹ ይልቅ ታማኝ መሆኑን በጓደኞቹ ፊት ገልጦ ነበር። ዛሬ ደግሞ በጓደኞቹ ፊት ትሁት መሆኑ ተገለጠ። ቅዱስ ጴጥሮስን ከጌታው ለመለየት ሰይጣን ጥያቄ አቅርቦ በክርስቶስ አገልግሎት ከስሞበት ቀርቶ ነበር (ሉቃ ፳፪፥፴፩-፴፪)። ቅዱስ ጴጥሮስ ከጠላት ክስ በክርስቶስ ስለዳነ እና ትሕትናን ስለተማረ ንስሐም ስለገባ የእግዚአብሔርን መንጋ ለመጠበቅ በቃ።

ግልገሎቼን ጠብቅ፥ በማለት በእምነታቸው ያልበሰሉትን ሕፃናት አእምሮ ምእመናንን ከስሕተት እንዲጠብቅ እንዲሁም በአካልና በእድሜም ሕፃናት የሆኑትን በእግዚአብሔር ቃል፣ በጥምቀት፣ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንዲያገኙ ያስተምር ዘንድ አደራ አለው።

ጠቦቶቼን ጠብቅ፥ በአእምሮም በአካልም በእድገት ላይ ያሉ ወጣቶችን ፈተና ይናወጥባቸዋል፤ በእውቀት በመጐልመስ ላይ ያሉት በክህደት ጎዳና እንዳይሄዱ፤ በሥጋቸው የሚጐለምሱም በዝሙት፣ ራስን ባለመግዛት፣ በትእቢት እንዳያድጉ በወንጌል ቃል እንዲጠብቃቸው አደራ ተባለ።

በጎቼን ጠብቅ፥ በእድሜም በእውቀትም ያደጉ የበለጸጉ ምእመናን በአምልኮተ እግዚአብሔር እንዲያድጉ ከፍቅረ እግዚአብሔር እንዳይለዩ እንዲጠብቃቸው ታዘዘ። በጎቹንም ለጠበቅ ጽኑእ መስዋእትነት መክፈል ስላለበት ጌታ የሚከተለውን ጠጣር ምሳሌ መስሎ የጴጥሮስን የወደፊት መከራ ገለጸለት። ምሳሌውም «አማን አማን እብለከ አመወሬዛ አንተ ለሊከ ትቀንት ኃቍከ ወተሐውር ኃበ ፈቀድከ ወአመሰ ልህቀ ታነስእ እዳዊከ ወባእድ ያቀንተከ ኃቍከ ወይወስደከ ኃበ ኢፈቀድከ» ማለትም «እውነት እውነት እልሃለሁ፥ አንተ ጐልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትሄድበት ትሄድ ነበር፤ ነገር ግን በሸመገልክ ጊዜ እጅህን ትዘረጋለህ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል» አለው። ይህን ያለው «በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው» ሲነግረው ነበር።

አንባቢ ሆይ፥ የክርስቶስን መንጋ ለመጠበቅ መስዋእትነትና ፍቅር እንደሚያስፈልግ ይገንዘቡ። ክርስቶስ ግልገሎቼን፣ ጠቦቶቼን፣ በጎቼን ጠብቅ ከማለቱ በፊት በአጽንኦት የጠየቀው «ትወደኛለህ ወይ?» በማለት ነበር። ሰው የተለያየ ችሎታ ቢኖረውም ያለ ክርስቶስ ፍቅር ለጌታ መንጋ ታማኝ እረኛ ሊሆን አይችልም። እውቀት፣ አንደበተ ርቱእነት፣ ቀናኢነት፣ ታታሪነት ቢኖረውም የክርስቶስ ፍቅር ከልቡ ውስጥ ከሌለ የወንጌል መልእክተኛው ሥራ የተሳካ ሊሆን አይችልም። እንዲሁም ሰው ለቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ለመሆን ከወሰነ እሱ ወደሚወደው ሳይሆን ሌሎች ወደሚወዱት መሄድ ግድ ነው። ራሱን አሳልፎ መስጠት ግድ ነው። ጴጥሮስ ወንጌልን በሚሰብክበት ጊዜ ለወንጌል ራሱን አሳልፎ በመስጠት የራሱን ፍላጐት በወንጌል በመለወጥ ደከመ። እግዚአብሔር አምላክ የእርሱን ፍላጐት እንድንሰራ እርሱን እንድንከተለው ለእኛም ጽናቱን ይስጠን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።